# ብቻህን አትሙት!!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ሰብእናህን ገፍፈው በገዛ አገርህ፤
በራብ በበሽታ በቁም ከገደሉህ፤
ባደ እጅህን አትሂድ ብቻህን አትሙት፤
እንዲሆንህ ለስንቅ  ጠላትክን ይዘህ ሙት!!።

በላቸው ግድየለም አሻፈረኝ እምቢኝ፤
ከንግዲህ ይበቃል በደሉ በዛብኝ፤
አልሞትም ብቻየን አልገባም መቃበር፤
ሌጣዬን አልሄድም ጠላቴን ሳልጨምር።

እምቢኝ በል  ግድየለም አትነዳ እንደከብት፤
ቢገሉህ አንዴ ነው ሁለቴ እንደሁ አትሞት፤
እሽታ ጭራሹን በደልን ያበዛል፤
ክብር አስገፍፎ አንገትን ያስደፋል፤
ሲደረግ በዋጉ ሲፈጸም በቦታው፤
ጥቃት ለማስወገድ እምቢታ ፍቱን ነው፤
እምቢታ ክብር ነው።

እምቢኝ ያያትህ ነው እምቢኝ ያባትህነው፤
አሻፈረኝ ማለት የናት የእህትህ ነው ፤
ውርደትን መመከት የጦቢያ ልምድ ነው፤
አንተጋ ሲደረስ ፍራቱ ምንድነው?!
እሽታው ምንድነው??!

አልከፍልም በል ግብር አልከፍልም በል ቀረጥ፤
እርም ነው ሃራም ነው አልገዛም በል ሸቀጥ፤
ከነሱ አትዋዋል ምንም ስምምነት፤
ከሃዲዎች ናቸው የላቸውም እምነት፤
ራቃቸው ናቃቸው ጭራሹን ትፋቸው፤
ከወገን ከአገር  ሆድ ወዳዶች ናቸው።

ሰብእናህን ገፈው በገዛ አገርህ፤
በራብ በበሽታ በቁም ከገደሉህ፤
ባዶእጅህን አቲድ ብቻህን አትሙት፤
መሞትህ ካልቀረ ጠላትክን ይዘህ ሙት!!

የሀል ያለህ ሲሉ ልጆችህ ተርበው፤
ጤፍህን በደላር ለባእድ ቸብቸበው፤
ተሟጠ ያንተ ቋት ባዶ ሆኖ ቤትህ፤
ይደራደራሉ ስንዴ ሊሸጡልህ።
በላቸው ግድየለም አሻፈረኝ እምቢኝ፤
ከንግዲህ ይበቃል በደሉ በዛበኝ፤
አልሞትም ሌጣዬን አልገባም መቃብር፤
ባዶ እጄን አልሄድም ጠላቴን ሳልጨምር።

እንዲሉ ሆነና « ያባይን ልጅ ጠማት »፤
በወያኔ ዘመን በወያኔ መንግሥት፤
መላው ወገናችን ቀኑ ጨልሞበት፤
ነጭ ጤፉ ቀርቶ ቦቆሎ አረረበት።
ሰብእናህን ገፈው በገዛ አገርህ፤
በራብ በበሽታ በቁም ከገደሉህ፤
ባዶ እጅህን አትሂድ አትሙት ብቻህን
መሞትህ ካልቀረ ይዘህ ሂድ ጠላትክን።

መስከረም 2 2001 ዓ.ም
በረሃብ፤ በበሽታና በፍትህ እጦት ለሚሰቃየው ወገናችን መታሰቢያ ትሁንልኝ